STATE OF WASHINGTON
DEPARTMENT OF SOCIAL AND HEALTH SERVICES
DIVISION OF CHILD SUPPORT (DCS)

# ድጋፍ ያለማድረግ የተነሳ ድጋፍ እንዲደረግ ማስገደጃ መረጃ

## Nonassistance Support Enforcement Information

(ምዕራፍ 26.18, 26.23, 34.05, 74.20, እና 74.20A RCW)

**ይህ ቅጽ በጥንቃቄ ይያዙት፣ ስለእርስዎ የልጅ ድጋፍ ጉዳይ በጣም አስፈላጊ የሕግ መረጃ ይዟል።**

**በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ እጃቸው ያለባቸው ወገኖች**

በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ እጃቸው ያለባቸው ሁለት ወገኖች አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ እና አሳዳጊ የሆነው ወይም በአካል ልጅ ይዞ የሚያሳድገው አሳዳጊ ናቸው። አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የድጋፍ ገንዘብ መክፈል ያለበት ግለሰብ ነው። አሳዳጊ ወላጅ ወይም በአካል ልጅ ይዞ የሚያሳድገው ወላጅ ልጆች አብረውት የሚኖሩት ግለሰብ ማለት ነው። ሁለቱም አሳዳጊ ሆነ አሳዳጊ ያልሆኑ ወላጆች የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን እና/ወይም የሕክምና ድጋፍ ለልጆች እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

- የሕክምና ድጋፍ በእርስዎ ትዕዛዝ ላይ የጤና ኢንሹራንስ ያልቀረበ ሆኖ ሲገኝ የሚጠየቅ የኢንሹራንስ ሽፋን ለሌላቸው የሕክምና ወጪዎች እና የሕክምና መድን ፕሪሚየም (አርቦን ክፍያ) ማለት ነው።

**የልጅ ድጋፍ መምሪያ**

የልጅ ድጋፍ መምሪያ (DCS) በመላው ስቴት ውስጥ የሚገኙ ቢሮዎች አሉት። DCS የልጅ ድጋፍ ጉዳዮችን ያስተዳድራል እና ያስፈጽማል። DCS የእርስዎን የድጋፍ ትዕዛዝ ለማስፈጸም እንዲችል፣ በትዕዛዙ ላይ እጃቸው ካለበት ወገኖች አንዱ በጽሑፍ የድጋፍ ማስፈጸም አገልግሎት እንዲሰጠው መጠየቅ አለበት።

የእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ በዋሽንግተን ግዛት የድጋፍ መዝገብ ቤት (የሚቀጥለውን ክፍል ይመልከቱ) በኩል ክፍያ እንዲፈጽም የሚጠይቅ ሆኖ ነገር ግን DCS ለአገልግሎቶች ጥያቄ ሳይቀርብለት ቢቀር፣ DCS የክፍያ አገልግሎቶች ብቻ (Payment Services Only (PSO)) ጉዳይ ለእርስዎ ይከፍትልዎታል። DCS ለ PSO ጉዳዮች የክፍያ ማስፈጸም ሂደት እና ሪኮርድ አያያዝ አገልግሎቶችን ብቻ ይሰጣል።

**የዋሽንግተን ግዛት የድጋፍ መዝገብ ቤት**

የዋሽንግተን ግዛት የድጋፍ መዝገብ ቤት (WSSR) ሪኮርዶችን የሚይዝ እና የድጋፍ ክፍያዎችን የሚያከፋፍል የ DCS አንድ ክፍል ነው። DCS ከሚከተሉት አንዱ ሲያጋጥም የእርስዎን የድጋፍ ትዕዛዝ ወደ WSSR ያስገባዋል።

1. በእርስዎ ድጋፍ ትዕዛዝ ላይ እጃቸው ካለባቸው ወገኖች አንዱ DCS የድጋፍ እንዲደረግ ማስገደጃ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ሲጠይቅ።
2. የእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የድጋፍ ገንዘብን በWSSR በኩል እንዲከፍል ሲያዝ።

ምን ማድረግ እንዳለብዎት

**አንድ ጊዜ DCS የድጋፍ እንዲደረግ ማስገደጃ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ከጠየቁ በኋላ፣ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፥**

1. ከአሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ በቀጥታ የተቀበሉትን ሁሉንም ክፍያዎች ወደ DCS መላክ። የእርስዎን ጉዳይ ለማስተናገድ DCS ሁሉም የክፍያ ሪኮርዶች ሊኖሩት ያስፈልገዋል። የDCS አገልግሎቶችን ለመጠየቅ ጥያቄ ከማቅረብዎ በፊት የድጋፍ ክፍያዎችን የተቀበሉ ከሆነ፣ ለDCS እነዚህን ክፍያዎች በመዘርዘር ዲክላራሲዮን መስጠት ይኖርብዎታል። ከአሳዳጊ ካልሆነ ወላጅ በቀጥታ ለተቀበሉት ክፍያዎች መረጃ ወደ DCS ሲልኩ፣ DCS የገንዘብ መጠኑን ወደ የእርስዎ DCS ዴቢት ካርድ ላይ ይጭናቸዋል ወይም የገንዘብ መጠኑን በቀጥታ ወደ የእርስዎ ተቀማጭ ገንዘብ የባንክ ሂሳብ ላይ ያስቀምጣቸዋል።
2. አድራሻዎን ወይም የስልክ ቁጥርዎን ከቀየሩ፣ ለDCS ያስታውቁ። DCS ይህን መረጃ ስለእርስዎ ጉዳይ እርስዎን ለማነጋገር ያስፈልገዋል። DCS ሕጋዊ ማስታወቂያዎችን በአንደኛ ደረጃ ደብዳቤ ፖስታ መላኪያ ሊልክ ይችላል።
3. ከአሳዳጊ ካልሆነው ወላጅ ጋር አብረው እንደገና መኖር ከጀመሩ ወይም ልጆቹ ሌላ ቦታ ለመኖሩ ከሄዱ በአስቸኳይ ለDCS ያስታውቁ። በተጠየቁ ጊዜ ለ DCS ተጨማሪ መረጃ መስጠ አለብዎት።
4. የእርስዎን የድጋፍ ገንዘብ እንዲቀበልልዎት ጠበቃ ወይም የግል ኤጀንሲ ከቀጠሩ ለDCS ያስታውቁ። ለDCS የጠበቃውን ወይም የግል ኤጀንሲውን ስም እና አድራሻ መስጠት አለብዎት። ለDCS ጠበቃው ወይም የግል ኤጀንሲው ምን እንደሚሰሩልዎት መንገር አለብዎት።
   a. ጠበቃው ወይም የግል ኤጀንሲው ገንዘቡን ለመቀበል በሚሞክሩበት ጊዜ DCS የእርስዎን የድጋፍ ገንዘብ ለመቀበል አይችል ይሆናል።
   b. የድጋፍ ትዕዛዝዎን ለመለወጥ ጠበቃ ከቀጠሩ፣ እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ ለአሳዳጊ ላልሆነው ወላጅ እና ለDCS ማስታወቂያ መስጠት አለባችሁ።
5. ለእርስዎ ጉዳይ የተሰጡ ሁሉንም የድጋፍ ትዕዛዞች ቅጂዎች ለDCS ይስጡ ወይም DCS እንዲያገኛቸው ያግዙ።

### ***ድጋፍ ያለማድረግ የተነሳ ድጋፍ እንዲደረግ ማስገደጃ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች***

ለድጋፍ ያለማድረግ የተነሳ ድጋፍ እንዲደረግ ማስገደጃ አገልግሎቶችን የሚጠይቁባቸው ልጆች ሕጋዊ የአብሮ በመኖር አሳዳጊነት መብት ከሌልዎት፣ ልጆቹን በስህተት ከሕጋዊ አብሮ በመኖር አሳዳጊ እንዳልነጠሉዋቸው ማረጋገጫ ቃልዎን መስጠት ይኖርብዎታል።

DCS በእያንዳንዱ በጀት ዓመት $35 በመቀበል ለእርስዎ DCS $550 በድጋፍ ገንዘብነት የሚልክልዎት ሲሆን ይህ የሚሆነው እርስዎ ከዚህ ቀደም ጊዜያዊ ድጋፍ ለችግረኛ ቤተሰቦች (Temporary Assistance to Needy Families (TANF))፣ የጎሳ ድጋፍ (Tribal TANF) ወይም ጥገኛ ልጆች ላላቸው ቤተሰቦች እርዳታ (Aid to Families with Dependent Children (AFDC)) ለማንም ልጅ ከዚህ ቀደም በጭራሽ ተቀብለው የማያውቁ ከሆነ ነው። የበጀት ዓመቱ በየአመቱ ኦክቶበር 1 ይጀምር እና በየዓመቱ ሴፕቴምበር 30 ላይ ያበቃል። DCS ለእርስዎ የመጀመሪያውን $550 ክፍያ ከላከ በኋላ ይህን ክፍያ ከእርስዎ የድጋፍ ክፍያዎች ላይ DCS $35 ተቀናሽ ያደርጋል። ልጆችዎ የተለያዩ አባቶች ስላሉዋቸው ከአንድ በላይ ጉዳይ ካልዎት፣ ከአንድ በላይ ዓመታዊ ክፍያ እንዲፈጽሙ ሊገደዱ ይችሉ ይሆናል። ከሌላ ስቴት TANF፣ Tribal TANF፣ ወይም AFDC ከተቀበሉ፣ እንደከሌላው ስቴት የሕዝብ እገዛ ሰጪ ኤጀንሲ የሚሰጥ በቃለ መሃላ የተደገፈ ቃል ወይም እንደ የእርስዎ የተረጋገጠ የድጋፍ ሪኮርዶች ቅጂን የመሰሉ ማስረጃዎች ለDCS መላክ አለብዎት። DCS ማስረጃውን እስከሚያገኝ ድረስ ክፍያውን ማስከፈላችንን እንቀጥላለን። የ $35 ክፍያን መክፈል ለቤተሰብዎ ችግርን የሚፈጥር ከሆነ የኮንፈረንስ ቦርድ በመጠየቅ ልዩ ሁኔታን ለ DCS መጠየቅ ይችላሉ፡፡

### ***የድጋፍ አስገድዶ ማስፈጸም አገልግሎቶች***

የድጋፍ ገንዘብ መጠኑን የሚጠቅስ የድጋፍ ትዕዛዝ ካልዎት፣ DCS ያንን የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን ለመቀበል ይሞክራል። DCS በእርስዎ ትዕዛዝ ላይ እንደተገለጸው ብዙውን ጊዜ ወለድ አስቦ አያስከፍልም። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የገንዘብ መቀበል እርምጃን ከመጀመሩ በፊት DCS ለሁለቱም በድጋፍ ትዕዛዙ ላይ እጃቸው ያለባቸው ወገኖች ማስታወቂያ መስጠት አለበት።

የድጋፍ ትዕዛዝ ከሌለዎት ወይም የእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ሁለቱንም የልጅ ድጋፍ እና የሕክምና ድጋፍ የማይመለከት ከሆነ፣ DCS ለሁለቱም በድጋፍ ትዕዛዙ ላይ እጃቸው ያለባቸው ወገኖች ማስታወቂያ ይሰጣል።

1. በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ፣ DCS እንደአስፈላጊነቱ የልጅ ድጋፍ እና የሕክምና ድጋፍ የገንዘብ መጠኖችን ይወስናል። DCS የልጅ ድጋፍ የገንዘብ መጠኑን የሚያሰላው በሁለቱም ወገኖች ጣምራ ገቢ እና በጉዳዩ ላይ ያሉ ልጆች ብዛትን ከግምት በማስገባት ይሆናል።

2. የእርስዎ ትዕዛዝ እያንዳንዱ ግዴታ የተጣለበት ወላጅ የኢንሹራንስ ሽፋን ማግኘት በሚቻልበት ጊዜ የጤና መድን ሽፋን ከወላጁ አሰሪ ወይም የሠራተኞች ማህበር ከወላጅየው መክፈል ያለበት የልጅ ድጋፍ ግዴታ ከ25 በመቶ በማይበልጥ እንዲከፈል የሚጠይቅ መሆን አለበት።

3. የሕክምና መድን ሽፋኑ በግዴታ የተጣለበት ወላጅ የማይሸፈን ከሆነ ትዕዛዙ በእርስዎ ወይም በመንግስት የተከፈለን የሕክምና ኢንሹራንስ አርቦን (ፕሪሚየም) ሊያካትት ይችላል።

የእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ የተወሰነ የድጋፍ ገንዘብን የማይጠቀስ ከሆነ እና ነገር ግን የገንዘብ መጠኑን ለማስላት ቀመር የሚሰጥ ከሆነ፣ DCS በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ እጃቸው ላለበት ለሁለቱም ወገኖች ***ያልተከፈለ የድጋፍ ዕዳ ማስታወቂያ*** ይሰጣል።

1. በዚህ ማስታወቂያ ላይ፣ DCS የተወሰነ የድጋፍ ገንዘብ መጠንን ያስቀምጣል። በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ያላችሁ ወገኖች DCS ያስቀመጠውን የገንዘብ መጠን በመቃወም አቤት ለማለት ትችላላችሁ።

2. DCS በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ላላችሁ ወገኖች የድጋፍ ገንዘብ መጠኑ ላይ ከስምምነት እንድትደርሱ ለማድረግ ይሞክራል።

አንድ ጊዜ የድጋፍ ገንዘብ መጠኑ ከተቀመጠ በኋላ እና DCS አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅን አሰሪ ሲያውቅ፣ DCS ለአሰሪው ***ለድጋፍ የገቢ ማስቆረጫ*** ማስታወቂያ ይልክለታል። ይህ ማስታወቂያ አሰሪው የድጋፍ ገንዘብ ከ አሳዳጊ ካልሆነው ወላጅ ገቢ ወይም ደመዎዝ ላይ እንዲቆርጥ ይጠይቃል። DCS አሳዳጊ ያልሆነውን ወላጅ አሰሪ ማንነት ማወቅ ሳይችል ሲቀር፣ DCS የእርስዎን የድጋፍ ገንዘብ ለመቀበል የደመዎዝ ወይም የገቢ ምንጩን ለማወቅ ይሞክራል።

የእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ለልጆቹ የሕክምና ድጋፍን የሚያካትት ከሆነ፣ DCS እነዚህን ግዴታዎች ለማስፈጸም ይሞክራል። DCS የሚወስዳቸው እርምጃዎች በእርስዎ ትዕዛዝ ላይ ባሉት ግዴታዎች ላይ የሚመረኮዙ ናቸው።

1. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያቀርብ፣ የመድን ዋስትና ላልተገባላቸው የሕክምና ወጪዎች፣ ተቀናሾች እና በጋራ የሚፈጸሙ ክፍያዎች የድርሻውን እንዲከፍል የተወሰነ መጠን እንዲወጣ የሚያዝ ወይም አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን ሳይኖረው በሚቀርበት ጊዜ ተጨማሪ ዶላር መጠን እንዲከፍል የሚጠይቅ ሲሆን፣ DCS ከነዚህ የሕክምና ድጋፍ ግዴታዎች አንዳቸውን ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያስደርጋል።

2. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን ለልጅዎት እንዲገባ የማይጠይቅ የድጋፍ ትዕዛዝ በሚኖርዎት ጊዜ፣ DCS ለእርስዎ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲሻሻል አቤት ለማለት ሊሞክር ይችላል።

3. እርስዎ የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያቀርቡ፣ የመድን ዋስትና ላልተገባላቸው የሕክምና ወጪዎች፣ ተቀናሾች እና በጋራ የሚፈጸሙ ክፍያዎች የድርሻዎን እንዲከፍሉ የተወሰነ መጠን እንዲያወጡ የሚያዝ ወይም የሌላኛውን ወላጅ የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን እርስዎ የጤና ኢንሹራንስ በማያቀርቡበት ጊዜ አርቦኑን (ፕሪሚየሙን) እንዲከፍሉ የሚጠይቅ የድጋፍ ትዕዛዝ በሚኖርዎት ጊዜ፣ አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የድጋፍ አስገድዶ ማስፈጸም አገልግሎቶችን በሚጠይቅበት ጊዜ DCS ከነዚህ ግዴታዎች አንዳቸውን ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያስደርጋል።

ለልጆቹ የጤና መድን ሽፋን ካልዎት፣ ለDCS የመድን ሽፋኑን ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። ከዚህ ጋር ተያይዞ የተላከልዎትን ***የአሳዳጊ ወላጅ የጤና ኢንሹራንስ መረጃ*** ቅጽ እንደየእርስዎ ማስረጃ ሞልተው መላክ ይችላሉ።

የጤና ኢንሹራንስ ሽፋን ኖርዎት DCS የእርስዎን የድጋፍ ትዕዛዝ የሕክምና ድጋፍ ግዴታዎች እንዲያስፈጽምልዎት የማይፈልጉ ከሆነ፣ ለDCS የሽፋኑን ማስረጃ በማቅረብ በጽሑፍ ለDCS የሕክምና ድጋፍ ግዴታዎችን እንዲያስፈጽምልዎት እንደማይፈልጉ መግለጽ አለብዎት።

እናት እና አባት በጭራሽ ተጋብተው የማያውቁ ከሆነ እና፥

1. አንዱ ወይም ሁለቱም ***የወላጅነት ማረጋገጫ*** ካልፈረሙ፣ የስቴት ወይም የጎሳ ፍርድ ቤት ሕጋዊ አባት ማን እንደሆነ መወሰን አለበት። DCS የእርስዎን ጉዳይ ወደ ዓቃቤ ሕግ፣ የጎሳ ፍርድ ቤት ወይም ወደ Office of the Attorney General እርምጃ እንዲወስድበት ይመራዋል።

2. ሁለቱም ***የወላጅነት ማረጋገጫ*** ከፈረሙ፣ DCS ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የድጋፍ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ያለው ሌላኛው ወገን DCS ይህን እንዲያደርግ ከጠየቀው፣ DCS እርስዎ ባይፈልጉትም ሙሉ የድጋፍ አስገድዶ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ተግባራዊ ያደርጋል።

በድጋፍ ትዕዛዙ ላይ ካሉ ወገኖች አንዳቸውም በዋሽንግተን ስቴት የማይኖሩ ከሆነ፣ DCS ከሚከተሉት ሁለቱም እውነት ከሆኑ የድጋፍ አስገድዶ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ይሰጣል።

1. በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ካላችሁ ወገኖች አንዳችሁም ብትሆኑ ከሌላ ስቴት የድጋፍ አስገድዶ ማስፈጸም አገልግሎቶች ተጠቃሚ አይደላችሁም።

2. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ መገኛ አድራሻ አለው። መገኛ አድራሻ ማለት በዋሽንግተን ከሚንቀሳቀሱ አሰሪዎች የሚገኙ ደመዎዞች፣ በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ቋሚ እሴቶች መኖር ወዘተን ያካትታል። DCS የድጋፍ ገንዘብን መቀበል እንዲችል አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ በዋሽንግተን ውስጥ አጥጋቢ የሆነ መገኛ አድራሻ ሊኖረው ይገባል።

አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ በሌላ ስቴት የሚኖር ከሆነ እና በዋሽንግተን ስቴት ምንም መገኛ አድራሻ የሌለው ከሆነ እና እርስዎ የሚኖሩት በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ከሆነ፣ DCS ከሚከተሉት አንዳቸውን ማድረግ ይችላል።

1. ለጉዳዩ ሕጋዊ መሰረት ለመመስረት እና በዋሽንግተን ስቴት ሕግ መሰረት የድጋፍ ገንዘቡን ለማግኘት መሞከር።

2. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የሚኖርበት ስቴት የድጋፍ ገንዘቡን እንዲቀበል መጠየቅ። ሌላኛው ስቴት ባለው ሕግ መሰረት እርምጃ ይወስዳል።

DCS ከአሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ያልተከፈሉ ውዝፍ የድጋፍ ክፍያዎችን አከፋፈል በተመለከተ ከስምምነት ላይ ይደርሳል። DCS ይህን ክፍያ በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ በተቀመጡ የድጋፍ ግዴታዎች እና በጉዳዩ ሳይከፈል በቀረው ውዝፍ አጠቃላይ ድምር ላይ በመመርኮዝ ይህን ክፍያ እንዲፈጸም ያደርጋል።

DCS ***ለድጋፍ ገቢ እንዲቆረጥ ማዘዣ*** እንዲሰጥ የሚፈቅድለት የድጋፍ ትዕዛዝ ካልዎት፣ DCS ማስታወቂያውን ለአሳዳጊ ላልሆነው ወላጅ አሰሪ (የሚታወቅ ከሆነ) ይሰጣል።

የእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ DCS ***ለድጋፍ ገቢ እንዲቆረጥ ማዘዣ*** እንዲሰጥ የማይፈቅድለት ከሆነ፣ DCS ***የድጋፍ ዕዳ እና የክፍያ መጠየቂያ ማስታወቂያ*** ለአሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ይሰጣል። ይህ ***የድጋፍ ዕዳ እና*** የክፍያ ***መጠየቂያ ማስታወቂያ*** የድጋፍ ገንዘቡን መጠን በመጥቀስ DCS ለድጋፍ ገቢ እንዲቆረጥ ማዘዣ እንዲሰጥ ስልጣን ይሰጠዋል።

1. እርስዎ በፍርድ ቤት ክፍያ እንዲፈጽሙ የተፈረደልዎት ተከፋይ ከሆኑ፣ DCS የድጋፍ ገንዘብ መጠኑን የሚጠቅሰው የማስታወቂያ ቅጂ ይልክልዎታል። ቅጂው ደርስዎት በማስታወቂያው ላይ በተጠቀሱት የገንዘብ መጠኖች የማይስማሙ ከሆኑ፣ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ።

2. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ በማስታወቂያው ላይ የተጠቀሱት ግዴታዎች የሚጠቅሱትን የድጋፍ ገንዘብ መጠን በመቃወም የኮንፈረስን ቦርድ (Conference Board) (መደበኛ ያልሆነ ችሎት) ጉዳዩን እንዲያየው ሊጠይቅ ይችላል። በኮንፈረንስ ቦርዱ ላይ መገኘት ይችላሉ።

3. እርስዎ ይግባኝ ብለው አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ደግሞ የኮንፈረንስ ቦርድ ጉዳዩን እንዲያየው ከጠየቀ፣ እርስዎ ይግባኙ እንዲቀጥል ወይም ጉዳዩ በኮንፈረንስ ቦርድ እንዲታይ ለመወሰን ይችላሉ።

የድጋፍ ትዕዛዝን በማስፈጸም ወይም በማሻሻል ሂደት ላይ፣ ለሁለቱም ወገኖች DCS የፅሑፍ ማሳሰቢያዎችን በደብዳቤ ሊያሳውቅ ይችላል። DCS እነዚህን ማስታወቂያዎች ለተከራካሪ ወገኖች በመጨረሻ የሚታወቅ አድራሻ ይልክላቸዋል። DCS ማስታወቂያ ከሰጥዎት፣ ለእርስዎ ተጨማሪ ማስታወቂያ መስጠት ሳያስፈልግ በእርስዎ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የመጨረሻ ትዕዛዝ ሊሆን ይችላል። ለድጋፍ ማዘዣ ማሻሻል የችሎት ቀን አንዱ ተከራካሪ ወገን በአካል መገኘት ካልቻለ ፍርድ ቤት ወይም የአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ (ALJ) ድጋፍን ለማሻሻል የሚቀርብ ማመልከቻን ተቀባይነት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል። የቀረው ወገን በመጨረሻ ለሚታወቅ አድራሻው የተላከውን ማስታወቂያ ስለማግኘቱ DCS ማረጋገጫ ባይሰጥ እንኳ ይህ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡DCS ለልጆችዎ እርስዎ ይዘው እንዲያሳድጉዋቸው ወይም እንዲጎበኙዋቸው ማስገደድ አይችልም።

**ውክልና**

DCS እና ሁሉም ከDCS ጋር የሚሰሩ Attorney General ቢሮዎች እና Prosecuting Attorney ቢሮዎች የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች መምሪያን (Department of Social and Health Services) ይወክላሉ። እነዚህ ቢሮዎች በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ያለን ማናቸውም ተከራካሪ ወገን አይወክሉም።

**የፍርድ ቤት ችሎቶች**

Chapter 34.05 RCW በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ያሉ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ በሚቆሙ ችሎቶች እንዲገኙ ይፈቅድላቸዋል። ተከራካሪ ወገኖች ችሎቱን በአካል በመገኘት ወይም በስልክ መሳተፍ ይችላሉ። ችሎቶች የእርስዎ የድጋፍ ገንዘብ መጠን ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል። በችሎት ላይ ሳይሳተፉ ቢቀሩ፣ ALJ ለእርስዎ ተጨማሪ ማስታወቂያ ሳይሰጥ በDCS ወይም በሌላኛው ተከራካሪ ወገን የቀረበለትን ጥያቄ ሊያጸድቀው ይችላል። የሕግ አማካሪ በችሎት ላይ እንዲቆምልዎት ማድረግ ይችላሉ።

**ቅነሳ**

የሕፃናት ሞግዚት ያልሆነ ወላጅ በእስር ቤት ፣ በወህኒ ቤት ወይም በማረሚያ ቤት ውስጥ ቢያንስ ለስድስት ወር ከታሰረ ወይም ከተፈረደበት እና የልጆች ድጋፍን የመክፈል አቅም ከሌለው የ Washington ሕግ ለጊዜው የልጆች ድጋፍን እንዲቀነስ ይፈቅዳል፡፡ ይህ ሂደት ቅነሳ ይባላል ፡፡ እርስዎ ፣ የሕፃናት ሞግዚት ያልሆነ ወላጅ ወይም DCS ቅነሳውን መጠየቅ ይችላሉ። ቅነሳው በጉዳይዎ ላይ ተፈፃሚ ከሆነ ፣ ከDCS የቅነሳውን ውሎች እና የማይስማሙ ከሆነ እያንዳንዱ ሰው ችሎት የመጠየቅ መብቱን የሚያብራራ ማሳወቂያ ይደርሰዎታል።

**የገንዘብ መሰብሰብ አገልግሎቶች**

DCS የሚከተለውን ለማድረግ ይሞክራል፥

1. አሁን ያለ እና ያለፈ ውዝፍ (ካለ) ድጋፍ ገንዘብን መሰብሰብ።
    - በአንዳንድ የተወሰኑ አስገዳጅ ሁኔታዎች፣ DCS አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ መክፈል ካለበት በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ከተጠቀሰው ወርሃዊ የድጋፍ ገንዘብ መጠን ያነሰ እንዲከፍል ጊዜያዊ ስምምነት ላይ ሊደርስ ይችል ይሆናል። ክፍያዎቹ DCS አሁን ያሉትን እና ያለፉትን ውዝፍ ዕዳዎች መልሶ ሙሉ በሙሉ ማስከፈል እንዲችል በጊዜ ሂደት እየጨመሩ ይሄዳሉ።
2. ወለድ እና ውዝፍ የድጋፍ ዕዳዎችን መሰብሰብ። ይህን DCS ሊያደርግ የሚችለው እርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ካልዎት ወይም የስቴት ወይም የጎሳ ፍርድ ቤት ዳኛ የፈቀደው የሚሰበሰብ የወለድ ገንዘብ ሲኖርዎት ብቻ ነው።
3. የልጅ እንክብካቤ ወጪዎችን ገንዘብ በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ከተጠየቀ ገንዘቡን መሰብሰብ።
4. የባለቤትነት (የጋብቻ) ድጋፍ ገንዘብ በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ከተጠየቀ ገንዘቡን መሰብሰብ። DCS የጋብቻ ድጋፍ የገንዘብ መጠኖችን አይወስንም።
5. የሕክምና ድጋፍ ግዴታዎችን ማስፈጸም። DCS ያልተከፈሉ የሕክምና ወጪዎችን (እንደ በጋራ የሚፈጸሙ ክፍያዎች፣ ተቀናሾች እና ፕሪሚየሞች ያሉ) ለልጆችዎ በትዕዛዙ መሰረት በChapters 74.20 and RCW 74.20A RCW ባሉ መልሶ ማስከፈያ ስልቶች በመጠቀም ገንዘቦቹን ለመሰብሰብ ይሞክራል። WAC 388-14A-1020 ኢንሹራንስ ያልተገባላቸው ወጪዎች ምን እንደሆኑ ያብራራል። DCS የጤና ኢንሹራንስ ግዴታዎችን ለማስፈጸም ወይም ግዴታ የተጣለበትን ወላጅ መክፈል ያለበትን የወጪዎች መሸፈኛ መጠን ልክ ሳያልፍ፣ ማለትም ከወላጅየው ለልጅ ድጋፍ መስጠት ያለበት ገንዘብ ግዴታ 25 በመቶ ሳይበልጥ የገንዘብ መዋጮውን ለማስከፈል ብሔራዊ የሕክምና ድጋፍ ማስታወቂያ ሊሰጥ ይችላል።
6. ልጆች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ካጠናቀቁ በኋላ ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድጋፍን ማስፈጸም። ስቴት ወይም የጎሳ ፍርድቤት ብቻ እንደዚህ ዓይነቱን ድጋፍ ማዘዝ ይችላል። DCS እንደዚህ ዓይነቱ ድጋፍ እንዲፈጸም መወሰን አይችልም።

በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትን እርምጃዎች DCS እንዲወስድ መጠየቅ የለብዎትም። DCS እንደ ጉዳይዎ የሚጠይቀው ሁኔታ እርምጃ ይወስዳል። ሆኖም ግን፣ የእርስዎን ድጋፍ ገንዘብ ለመቀበል ለDCS የሚረዳው አዲስ መረጃ ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል። ካገኙ፣ ለDCS መንገር አለብዎት። በሁሉም ከDCS ጋር በሚያደርጉዋቸው የደብዳቤ መጻጻፎች የሚከተሉትን ያካትቱ።

1. የእርስዎ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የጉዳይ ፋይል ቁጥር።
2. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ስም እና ማህበራዊ ዋስትና ቁጥር (የሚታወቅ ከሆነ)።

**የDCS አገልግሎቶችን ማስቆም**

DCS ሙሉ የገንዘብ መሰብሰብ አገልግሎቶቹን እንዲያቆም ከፈለጉ፣ በጽሑፍ DCSን መጠየቅ አለብዎት። አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የድጋፍ ገንዘቡን በWSSR በኩል እንዲፈጽም የሚያዝ የድጋፍ ትዕዛዝ ካልዎት፣ DCS ሙሉ የገንዘብ መሰብሰቦችን አገልግሎት መስጠቱን በማቆም የእርስዎን ጉዳይ ወደ PSO ይመራውና ይህንኑ ለአሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ያሳውቃል። የእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ክፍያ በWSSR በኩል እንዲፈጸም የማያዝ ከሆነ፣ DCS የእርስዎን ጉዳይ ይዘጋዋል።

እርስዎ ወይም የእርስዎ ልጆች አሳዳጊ ካልሆነው ወላጅ ጋር አብራችሁ እንደገና መኖር ከጀመራችሁ፣ DCS አሁን ያልዎትን የድጋፍ ገንዘብ መሰብሰቡን ያቆማል። DCS እያገኙ ላሉት አገልግሎት ላይ ማናቸውም ለውጥ ሲደረግ ያሳውቅዎታል።

**የፌደራል የገቢ ግብር ማስመለሻ (Federal Income Tax Refund Offset)፣ አስተዳደራዊ እርምጃ (Administrative Offset) እና የፓስፖርት መከልከል**

DCS አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ያልተከፈል ውዝፍ የድጋፍ ዕዳ በሚኖረው ጊዜ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች የእርስዎ ጉዳይ ሲያሟላ ለአገር ውስጥ ገቢ አገልግሎቶች (Internal Revenue Service (IRS)) ያሳውቃል፥

1. DCS አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅን የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር አውቋል።
2. ያልተከፈለው ውዝፍ የድጋፍ ገንዘብ ዕዳ በድጋፍ ትዕዛዝ መከፈል የነበረበት ነው።
3. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ከ $500.00 ወይም ከዛ በላይ የሆነ ያልተከፈለ ውዝፍ የድጋፍ ገንዘብ ዕዳ አለበት። DCS ያልተከፈለ ውዝፍ የድጋፍ ዕዳ መጠንን መወሰን ካልቻለ፣ DCS የእርስዎን ጉዳይ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ያለውን የገንዘብ መጠን ያህል በመቁጠር DCS ዕዳውን ሊወስነው ይችላል።

IRS ያልተከፈለ የልጅ ድጋፍ ገንዘብ ዕዳን ለመክፈል ለ DCS አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅን የታክስ ተመላሽ ገንዘቦችን ይልክለታል።

አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ጣምራ የታክስ ተመላሽ ገንዘብ እንዳለው ፋይል ካቀረበ፣ DCS ለእርስዎ ገንዘቡን ከመላኩ በፊት ተመላሽ ገንዘቡን ለስድስት ወራት ያክል ሊያቆየው ይችላል። DCS የታክስ ተመላሽን መያዝ የሚፈቅደው ሌላኛው ጣምራ የታክስ ተመላሽ ገንዘብ ያለው ወገን ከተመላሽ ገንዘቡ ሊደርሰው የሚገባውን የገንዘብ ድርሻ እንዲጠይቅ ጊዜ ለመስጠት ነው።

ሌሎች አሳዳጊ ላልሆነው ወላጅ በፌደራል መንግስት መከፈል ያሉበት ገንዘቦች ያልተከፈሉ ዕዳዎችን ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ቢያንስ $2,500.00 ዕዳ ካለበት፣ የፌደራል መንግስቱ አሳዳጊ ላልሆነው ወላጅ ፓስፖርት እንዳይሰጠው ሊከለክል ይችላል።

**የክፍያ ማከፋፈል**

የድጋፍ ክፍያዎችን ማከፋፈል በተመለከተ ጥብቅ የሆኑ የፌደራል እና የስቴት ደንቦች አሉ። DCS የክፍያ የተፈጸመበትን ቀን እንዴት የድጋፍ ገንዘብን ተፈጻሚ ለማድረግ እንደሚችል ይጠቀምበታል። ማናቸውም በድጋፍ ትዕዛዙ ጉዳይ ላይ ያሉ ወገኖች ክፍያው የሚሸፍነውን የጊዜ መጠን መምረጥ አይችሉም።

1. DCS በየወሩ የመጣን ማናቸውም ገንዘብ፣ ከIRS ከመጀመሪያው እስከ አሁን ያለው ድጋፍ የሚሰጥበት ወር የመጣ የታክስ ተመላሽ ገንዘብ በስተቀር ተፈጻሚ ያደርጋል። IRS ክፍያዎች ላልተከፈሉ ውዝፍ የልጅ ድጋፍ ዕዳዎች ክፍያ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

2. DCS ከዚህ ቀደም እንደ ለአካልመጠን ያልደረሱ ልጆች አሳዳጊ TANF፣ Tribal TANF፣ ወይም AFDC ገንዘቦችን ተቀብለው የማያውቁ ከሆነ፣ ዓመታዊ የአገልግሎት ክፍያ $35 ከገንዘብዎ ላይ ተቀናሽ ያደርጋል። DCS ክፍያውን ከድጋፉ ገንዘብ $550 ለእርስዎ መከፈል በኋላ ከኦክቶበር 1 እና ከሴፕቴምበር 30 መካከል ባሉት ጊዜያት በዓመት አንዴ ክፍያውን ይሰበስባል።

3. DCS አሁን ካለው የድጋፍ ገንዘብ መጠን የበለጠ ገንዘብ ከተቀበለ፣ DCS ተጨማሪውን ገንዘብ ባለፈው ያልተከፈለ ውዝፍ ዕዳ ላይ ተከፋይ ያደርገዋል።

4. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ከአንድ ቤተሰብ በላይ አሁን ያለ የድጋፍ ገንዘብ ዕዳ ካለበት፣ DCS ገንዘቡን ወደ ሁሉም መፈጸም ያለባቸው የድጋፍ ግዴታዎች በመጀመሪያ ተከፋይ ካደረገ በኋላ የቀረውን ላለፈው ያልተከፈል ውዝፍ ዕዳ መክፈያ ያውለዋል። እርሶም ሆኑ አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ እንዴት DCS ክፍያዎችን እንደሚያከፋፍል መምረጥ አትችሉም።

   - ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው አንድ በልዩ ዓይን የሚታይ ሁኔታ አለ። አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ወደ PSO ጉዳዮች የሚደረጉ ክፍያዎችን አከፋፈል ሁኔታ ሊመርጥ ይችላል። PSO እንደዚህ የመሰሉ ጉዳዮችን ወደ DCS በመላክ የሪኮርድ አያያዝ እና የክፍያ ማከፋፈል ስራዎችን እንዲሰራ የሚያደርግ ቢሆንም የድጋፍ ትዕዛዝ አስገድዶ ማስፈጸም ስራን አይሰራም።

DCS አሁን ያሉ የድጋፍ ክፍያዎችን ለእርስዎ ይልካል። በቀጥታ ተቀማጭ እንዲደረግልዎት ከፈረሙ፣ DCS ክፍያዎችን በቀጥታ ወደ የእርስዎ የባንክ ሒሳብ በኤሌክትሮኒካዊ የገንዘብ ዝውውር (Electronic Funds Transfer (EFT)) ያስቀምጥልዎታል።

**ማሳሰቢያ፥ በቀጥታ ገንዘብዎ እንዲቀመጥ ፈቃድ ካልሰጡ፣ DCS በአውቶማቲክ የእርስዎን የተቀመጠ እሴት(stored-value) Visa የዴቢት ካርድ፣** በሌላ ስሙ **DCS** የዴቢት ካርድ ወደሚባለው ገንዘብዎን ይልክልዎታል። የDCS ዴቢት ካርድ ካልዎት፣ DCS የእርስዎን የልጅ ድጋፍ ገንዘብ ከባንክ ሒሳብዎ ይልቅ ወደዚህ ካርድ ይልክልዎታል። በአብዛኛው ሁኔታ፣ የልጅ ድጋፍ ክፍያዎች በባንክ ሒሳብዎ ላይ ወይም በእርስዎ የDCS ዴቢት ካርድ ላይ DCS ክፍያዎቹን ለእርስዎ በፈጸመ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። የDCS ዴቢት ካርድን በማናቸውም VISAን የሚቀበሉ ቦታዎች እና አውቶሜትድ ቴለር ማሽኖች ኤቲኤሞች (Automated Teller Machines) መጠቀም ይችላሉ። ስለኤሌክትሮኒካዊ ክፍያዎች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ክፍያ ለመቀበል ስላሉዎት ሌሎች አማራጮች ለማወቅ ወደ 800-468-7422 መደወል ወይም በኦንላይን www.dshs.wa.gov/dcs ማየት ይችላሉ።

ውዝፍ ያልተከፈሉ ዕዳ ክፍያዎች ለእርስዎ ሊሰጡ ላይሰጡም ይችላሉ።

1. እርስዎም ሆኑ ልጆችዎ የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ ተቀብላችሁ የማታውቁ ከሆነ፣ DCS ገንዘቡን ይልክልዎታል።

2. የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ የተቀበሉ እና ለማናቸውም የአስተዳደር አካል ቀሪ ዕዳ የሌለብዎት ከሆነ፣ DCS ገንዘቡን ይልክልዎታል።

3. ባለፈው ጊዜ የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ የተቀበሉ ከሆነ፣ DCS ያልተከፈለ ውዝፍ የድጋፍ ዕዳን እርስዎ የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ መቀበል ካቆሙበት ጊዜ ጀምሮ እንደሚከተለው ያከፋፍላል፥

   a. በመጀመሪያ፣ ወደማናቸውም ለስቴት መከፈል ያለባቸው ያልተከፈሉ የድጋፍ ዕዳዎች።

   b. ሁለተኛ፣ ከኦክቶበር 1፣ 1997 በኋላ እና ከኦክቶበር 1፣ 2008 በፊት በተሰጠ ትዕዛዝ ላልተከፈሉ ወደማናቸውም ለስቴት መከፈል ያለባቸው ያልተከፈሉ የድጋፍ ዕዳዎች፣ የሚላክ ሲሆን ይህ የገንዘብ መጠን ከዚህ በታች ለተብራራው በቋሚነት የተመደበ ያልተከፈለ የድጋፍ ውዝፍ አካል ያልሆነ።

   c. ሶስተኛ፣ ለልጆች እርስዎ መከፈል የነበረብዎት ያልተከፈለ ውዝፍ የሕክምና ዕዳ።

   d. አራተኛ፣ ከኦክቶበር 1፣ 1997 በፊት ለስቴት መከፈል ላለበት የሕዝብ ድጋፍ ያልተከፈለ ውዝፍ ዕዳ፣ ወይም ከዚህ ቀን በኋላ በዛ ወር ላይ የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ ለእርስዎ ስለተከፈለ።

   e. አምስተኛ፣ ለስቴት የተመደበ ማናቸውም የልጆች ያልተከፈለ የሕክምና ድጋፍ ውዝፍ ዕዳ።

   f. ከIRS ላለፈ ያልተከፈል ውዝፍ የድጋፍ ዕዳ የተከፈሉ ለስቴት የተመደቡ የሕክምና ድጋፍ ክፍያዎች ለእርስዎ ያልተከፈሉ ማናቸውም የድጋፍ ውዝፍ ዕዳዎች ተከፋይ ከመደረጋቸው በፊት።

4. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ከአንድ ቤተሰብ በላይ ያልተከፈለ ውዝፍ ዕዳዎች ያሉበት ከሆነ፣ DCS ገንዘቡን በእነዚህ ቤተሰቦች መካከል አመጣጥኖ ያከፋፍላል።

**ገንዘብ ማስመለስ**

ከልክ በላይ ክፍያዎች እና በስህተት ክፍያዎች ለእርስዎ ሲፈጸሙ በRCW 26.23.035(3) እና 74.20A.270 መሰረት፣ DCS ገንዘቡን ከእርስዎ ያስመልሳል።

1. የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ DCS ለእርስዎ የላከልዎትን ክፍያ ተመላሽ ማድረግ አለብዎት፥
   a. DCS በስህተት ገንዘብ ቢልክ።
   b. DCS አሳዳጊ ያልሆነ ወላጅ መክፈል ካለበት የገንዘብ መጠን የበለጠ ገንዘብ ከላከልዎት፣ ይህ በተጨማሪ ትርፍ ክፍያ (overpayment) በመባል ይታወቃል።
2. የክፍያ አገልገሎት ብቻ ጉዳይ ካለዎት DCS በመጀመሪያ በትርፍ ክፍያ የተላኩ ገንዘቦችን እና በስህተት የተፈጸሙ ክፍያዎችን ለእርስዎ የሚደረጉ ክፍያዎች ላይ በመቀነስ ተመላሽ እንዲሆኑለት ያደርጋል። RCW 26.23.035(3) ይህ እርምጃ ለእርስዎ ማስታወቂያ መስጠት ሳያስፈልግ እንዲወሰድ ይፈቅዳል።
   a. DCS በአውቶማቲክ አሁን ካለው የድጋፍ ክፍያዎች ላይ 10 በመቶ በመያዣነት ይይዛል።
   a. DCS በአውቶማቲክ አሁን ካለው የድጋፍ ክፍያዎች ላይ ላልተከፈሉ ውዝፍ የድጋፍ ዕዳዎች 100 ፐርሰንት በመያዣነት ይይዛል።
3. DCS ለእርስዎ በትርፍ ክፍያነት ለተላኩ ገንዘቦች እና በስህተት የተፈጸሙ ክፍያዎች ማስመለሻነት በRCW 74.20A.270 የተፈቀዱ ሌሎች የገንዘብ ማስመለሻ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል። ይህ በDCS በኩል የድጋፍ ክፍያዎችን መቀበልዎን ቢያቆሙ እንኳ ተፈጻሚ ይሆናል። DCS ይህን አማራጭ ከመረጠ፣ DCS በእርስዎ ላይ ማስታወቂያ ያወጣል። ምንም ተቃውሞ ካልደረሰው፣ DCS የሚከተሉትን እንዲያደርግ ይፈቀድለታል፥
   a. ለእርስዎ አሰሪ ወይም የእርስዎ ንብረት ላለው ሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለድጋፍ የገቢ ማስቀረጫ ትዕዛዝ ይልካል። ትዕዛዙ/ማስታወቂያው አሰሪው ወይም ሌላው ግለሰብ ወይም ድርጅት ለእርስዎ በስህተት እና/ወይም በትርፍ ክፍያ ለተፈጸመ ክፍያ ከደመዎዝዎ፣ ከገቢዎ እና ከንብረትዎ ላይ ገንዘቡን ተቀናሽ እንዲያደርግ ያዛል።
   b. በእርስዎ የቤት እና የግል ንብረት ላይ ሐራጅ እንዲወጣ ፋይል ይከፍታል።
   c. ማናቸውም ለ DCS ገንዘብ ማስመለሻ የተፈቀዱ እርምጃዎችን በChapters 26.09, 26.18, 26.23, እና 74.20 RCW መሰረት ይወስዳል።

**የጎሳ መረጃ**

DCS እና ጎሳው በተለየ መንገድ ካልተስማሙ በቀር፣ በዚህ ቅጽ ላይ የተዘረዘሩት የDCS አስገድዶ ማስፈጸሚያ እና የገንዘብ አሰባሰብ እርምጃዎች ለጎሳዎች ለሚሰሩ ሰራተኞች፣ በጎሳ ይዞታነት ለሚተዳደሩ ንግዶች፣ ወይም በሕንዳዊያን በተያዙ የተከለሉ ንግዶች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም። አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የሕንዳዊ ጎሳ፣ በሕንዶች ይዞታነት በተከለለ ንግድ ሥራ ሠራተኛ ከሆነ፣ DCS የሚከተሉትን ሊያደርግ ይችላል፥

1. የእርስዎን የድጋፍ ትዕዛዝ ጎሳው እንዲያስፈጽም መጠየቅ። DCS ይህን ሊያደርግ የሚችለው የዋሽንግተን ስቴት እና ጎሳው ይህን ለማድረግ የተስማሙበት የአፈጻጸም ስርዓት ካላቸው ነው።
2. የእርስዎን የድጋፍ ትዕዛዝ ለማስፈጸም ወይም ለማስከበር በጎሳው ፍርድ ቤት ፋይል መክፈት። DCS በጎሳ ፍርድ ቤት እርምጃ ለማስወሰድ ፋይል ከከፈተ፣ DCS በዋሽንግተን ስቴት እና በሕንድ ጎሳ መካከል የተቀመጡ የአፈጻጸም ስምምነቶችን ሊጠቀም ወይም የጎሳ ፍርድ ቤቱ የአፈጻጸም ስርዓትን ሊጠቀም ይችላል።

DCS የእርስዎን ጉዳይ ወደ የጎሳ ጉዳይ አስገድዶ ፈጻሚ አካል ከሚከተሉት አንዱ ከእርስዎ ጉዳይ ጋር ተስማሚነት ካላቸው ሊመራው ይችላል።

1. በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ካላችሁ ወገኖች አንዳችሁ ወይም ከልጆቻችሁ መካከል አንዱ የሕንድ ጎሳ አባላት ከሆናችሁ።
2. አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የሕንዳዊ ጎሳ፣ በጎሳ ይዞታነት ባለ የንግድ ሥራ ወይም በሕንዶች ይዞታነት በተከለለ ንግድ ሥራ ሠራተኛ ከሆነ።
3. በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ካላቸሁ ወገኖች አንዳችሁ በኮርፖሬት የልጅ ድጋፍ ሂደት ወይም ስምምነት ስር የመድን ሽፋን ካላችሁ።
4. በእርስዎ የድጋፍ ትዕዛዝ ላይ ካላችሁ ወገኖች አንዳችሁ ከTribal TANF ወይም Tribal child የድጋፍ ፕሮግራም አገልግሎቶችን የምትቀበሉ ከሆናችሁ።
5. የእርስዎ ጉዳይ ሌሎች ጎሳ ነክ ጉዳዮችን የሚመለከት ከሆነ።

**የልጅ ድጋፍ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ሕጎች እና ፖሊሲዎች**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የRevised Code of Washington (RCW) ምዕራፎች እና የWashington Administrative Code (WAC) ሕጎች DCS የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ያስተዳድራሉ።

Chapter 26.09 RCW
Chapter 26.18 RCW
Chapter 26.21A RCW
Chapter 26.23 RCW
Chapter 74.20 RCW
Chapter 74.20A RCW

Chapter 388-14A WAC

ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አለመቻል ሕግ ለልጅ ድጋፍ ዕዳ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል። ተገቢነት ካለው፣ አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ የአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አለመቻል ሕግን እንደ መከላከያ ሊጠቀም እና ከእንግዲህ ምንም ዕዳ እንዳይኖረው ሊያስደርግ ወይም የተወሰነ የድጋፍ ዕዳውን ሊያስቀንስ ይችላል።

**የስልክ ጥሪዎች**

ስለእርስዎ ጉዳይ መረጃ ለማግኘት ወደ "KIDS" አውቶሜትድ የስልክ ስርዓት በስልክ ቁጥር 800-442-5437 ይደውሉ። ይህን ስርዓት በተቻልዎት መጠን ሁሉ ይጠቀሙ። የ "KIDS" ስርዓት ሊያስተናግደው የማይችለው ነገር ካጋጠምዎት፣ የእርስዎን ጉዳይ ወደያዘው የDCS ቢሮ ይደውሉ። በእርስዎ ጉዳይ ላይ ገንዘብ ለመሰብሰብ ከሚሰራው ሥራ ላይ የስልክ ጥሪዎች ጊዜ እንደሚቀንሱ ያስታውሱ። የስልክ ጥሪዎችን ቁጥር መቀነሱ DCS እርስዎን የተሻለ እንዲያገለግልዎት ያስችለዋል።

DCSን ማነጋገር ካለብዎት፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስልክ ቁጥሮች ይጠቀሙ። ነጻ የስልክ መስመሩን እባክዎ ለረዥም ርቀት ጥሪዎች ብቻ ይጠቀሙ። ለንግግር እና መስማት የተሳናቸው የ TTY/TDD አገልግሎቶችን ማግኘት ይቻላል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሲያትል፥ | (206) 341-7000 ወይም (800) 526-8658 | ቫንኩቨር፥ | (360) 696-6100 ወይም (800) 345-9984 |
| ታኮማ፥ | (253) 597-3700 ወይም (800) 345-9976 | ዌንታቼ፥ | (509) 886-6800 ወይም (800) 535-1113 |
| ኤቨርት፥ | (425) 438-4800 ወይም (800) 729-7580 | ያኪማ፥ | (509) 249-6000 ወይም (800) 441-0859 |
| ስፖካኔ፥ | (509) 363-5000 ወይም (800) 345-9982 | ኦሎምፒያ፥ | (360) 664-6900 ወይም (800) 345-9964 |
| ኬንዊክ፥ | (509) 374-2000 ወይም (800) 345-9981 | | |

ስለ ኤሌክትሪኒካዊ ክፍያዎች መረጃ ለማግኘት ወደ 800-468-7422 ይደውሉ ወይም የDCS የድርጣቢያን www.dshs.wa.gov/dcs ላይ ይጎብኙ። የእርስዎን ጉዳይ የክፍያ ታሪክ ለማየት መስመር ላይ (ኦንላይን) በ https://secureaccess.wa.gov መመዝገብ ይችላሉ።

ማንም ሰው በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ ምንጭ ሃገሩ፣ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ ዕድሜ ወይም የአካል ጉዳተኝነት የተነሳ የሥራ ቅጥር፣ አገልግሎቶች በማግኘት፣ ወይም በማናቸውም የፕሮግራሙ እንቅስቃሴዎች መድልዎ ሊፈጸምበት አይችልም። ይህ ቅጽ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በተለያዩ ቅርጸቶች ሊገኝ ይችላል።